# ክርስቲያናዊ ሕይዎትና የክርስቲያን የፊልም፣ የቴአትር፣ የድራማ ተዋንያን የትወና ነጻነት እስከምን ድረስ?

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ቴሌቪዥን (ምርዓየ ኩነት) የትንሣኤን በዓል ምክንያት በማድረግ ከተዋንያን ይገረም ደጀኔ፣ ትግሥት ግርማ እና ንብረት ገላው ጋር የበዓል እንግዳ በማድረግ ቆይታ አድርጎ ነበር፡፡ የዝግጅቱ ጋባዥ (host) መምህር ማርቆስ በማለት ራሱን ያስተዋወቀው ሰው ያቀረበላቸው ጥያቄና እነሱም ከእልህ ጋራ የመለሱት መልስ ትኩረቴን ስለሳበውና በእጅጉ ስሕተት ሆኖ ስላገኘሁት እጽፍበት ዘንድ ግድ አለኝና ነው ይሄንን ጽሑፍ የጻፍኩት፡፡

ጣቢያው ወይም አዘጋጁ ዝግጅቱን ሙሉውን አላቀረበውም፡፡ ቀሪው ክፍል መቼ እንደሚቀርብም አልተናገረም፡፡ ጣቢያው አመሉ ነው፡፡ ደረጃውን የጠበቀ አሠራር አይደለም እየተከተሉ ያሉት፡፡ የትኛውም ዝግጅት መቼ እንደሚቀርብ አይታወቅም፡፡ ደስ ባላቸው ሰዓት የአንድ ዝግጅትን ቀዳሚ ክፍል ካቀረቡ በኋላ ቀሪ ክፍል እንዳለውና ያ ቀሪ ክፍሉም መቼ እንደሚቀርብ እንኳ ሳያሳውቁ ከፊሉን አቅርበው ያቋርጡትና ሌላ ዝግጅት ደሞ ያቀርባሉ፡፡ ቀሪውን ክፍል ለመከታተል የምትፈልጉ ከሆነ ለቀናት ዓይናቹህን ከጣቢያው ማንሣት አይኖርባቹህም፡፡ ካለበለዚያ ያመልጣቹሀል፡፡

እዚያ ቦታ ምን ዓይነት የብቃትና የችሎታ ማነስ ችግር ያለባቸው፣ የብዙኃን መገናኛ ስርጭት እንዴት እንደሚሠራ፣ እንዴት መሔድ እንዳለበትና ምን ዓይነት ሥነሥርዓት (discipline) እንዳለው ምንም የሚያውቁት ነገር የሌላቸው፣ ለቦታው ፈጽሞ የማይመጥኑ ሰዎች ተሰግስገው ጣቢያውን እየመሩ እንዳሉ ይሄ አንዱ ማሳያ ነው፡፡ የብቃትና የችሎታ ማነስ ችግሮቻቸው ከአንድ የብዙኃን መገናኛ እንደሚጠበቀው ለዝግጅቶቻቸው ስኬጁልድ ሆነው ባለመገኘታቸው (ቀድሞ በተያዘ የጊዜ አጠቃቀም) ባለመመራታቸው ብቻ ሳይሆን በሚያቀርቧቸው ዝግጅቶች ሁሉ በጉልህ የሚስተዋል ጉዳይ ነው፡፡

እዚያ ውስጥ ያሉ በሙሉ ያልጠነቀቁ ሰዎች ናቸው፡፡ እንዳልኳቹህ ያለመጠንቀቃቸውን በየ ዝግጅቶቻቸው ትታዘቡታላቹህ፡፡ ያው ይሄና ተመሳሳይ ችግሮች በዚህ በቤተክርስቲያኗ የቴሌቪዥን (የምርዓየ ኩነት) ጣቢያው ብቻ ያለ ሳይሆን በአጠቃላዩ የቤተክርስቲያኗ መዋቅር ተንሰራፍቶ የበቁት፣ የጠነቀቁት፣ አዋቂዎች፣ ሊቃውንቱ እየተገፉ፣ እየተገለሉ ቦታዎች የሚያዙት በፖለቲካ ታማኝነት ብቻ በመሆኑ ቤተክርስቲያኗን ለከፍተኛ አደጋና ስብራት የዳረገ ስር የሰደደ ችግር ከሆነ ሁለት ዐሥራት ዓመታትን ያሳለፈ ችግር ነው፡፡ መድኃኔዓለም ክርስቶስ መፍትሔ ይስጠው እንጅ፡፡

እናም በዚህ ችግር ምክንያት ከነኝህ ከላይ ከጠቀስኩላቹህ የተውኔት (የቴአትር) ፣ የፊልም (የምትርኢት) ፣ የድራማ (የትውንተ ኩነት) ተዋንያን ጋር የተደረገውን ቃለ ምልልስ ወይም ውይይት ቀሪ ክፍል ልመለከተው አልቻልኩም፡፡ በዚህ ምክንያት ይህ ጽሑፌ በተከታተልኩት በቀዳሚው ክፍል ላይ ተዋንያኑ በተናገሩት ነገር ላይ ያተኮረ ለመሆን ተገዷል፡፡

ተዋንያኑ እንደተናገሩት ሕዝቡ በሚተውኗቸው ገጸባሕርያት ዓይን እያሰባቸው እንደ ክርስቲያንነታቸው ቤተክርስቲያን ለመሳለም ሔደው እዚያ በሚያገኛቸው ጊዜና "አገልግሎት" ላይ ሲያያቸው እንደሚቃወማቸው ይሄም ትክክል አለመሆኑን "እዚያ ላይ የምናንጸባርቀው ማንነት የገጸ ባሕርያቱ ማንነት እንጅ የእኛ የግል ሕይዎት ወይም ትክክለኛ ማንነት ስላልሆነ በሕዝቡ እየደረሰብን ያለው መገለልና ያልተገባ የንቀትና የመጸየፍ አመለካከት ፈጽሞ ትክክል አይደለም!" በማለት "የኢየሱስ" ያሉትን ፊልም (ምትርኢት) እና ሌላም ምሳሌ እየጠቀሱ ብሶታቸውን በጣም በምሬት አሰምተዋል፡፡

የዚህን ጊዜ የዝግጅቱ ጋባዥ "የገጸ ባሕርያቱ ነው እየተባለ ከእናንተ ውስጥ ቆራቢ ቢኖርና ሲተውን ቢራ ጠጣ፣ ሲጋራ አጭስ፣ .....ጫት ቃም ቢባል ሊያደርገው ነው ወይ?" ብሎ ሲጠይቃቸው ከክርስትናቸው ጋር ሊቃረን እንደማይችል ሽንጣቸውን ገትረው በመከራከር "ይሄ የገጸ ባሕርዩ ማንነት እንጅ የኔ የግሌ አይደለምና በግል ሕይዎቴ የማደርገው አይሁን እንጅ በገጸባሕርይ ውስጥ ከሆነ ችግር አለው ብየ ስለማላምን፣ ከክርስትናየ ጋር ይቃረናል ስለማላስብ አዎ አደርገዋለሁ!" ሲሉ

እያንዳንዳቸው መልሰዋል፡፡

በርግጥ የዲያቆኑ ጥያቄ ያልበቃ ወይም ያልበሰለ ጥያቄ ነው፡፡ ሲጀመር ቆራቢ የሆነ ሰው ቢራ አይጠጣም ተብሎ አያውቅም፡፡ ነው ወይስ ካህናቱ ቤተምርፋቅ ውስጥ የክርስትናውን፣ የተዝካሩን፣ የዝክር ማኅበሩን ጠላ፣ ጠጅ፣ ቢራ ሲጠጡ ዓይቶ አያውቅም???

ጫት ሲጋራ ላለውም አንዳንዶቹ እንደሚሉት ተዋንያኑ "ጫት መቃም፣ ሲጋራ ማጨስ ኃጢአት ነው ያለው ማን ነው? ፣ የትኛውስ መጽሐፍ ነው? ቅዱስ ጳውሎስ በሥጋ ገበያ የሚሸጠውን ሁሉ ከሕሊና የተነሣ ሳትመራመሩ ብሉ ምድርና በሷ የሞላበት ሁሉ የጌታ ነውና ቆሮ. 10፤23" ብለው ቢያፋጥጡት ምን ሊመልስ ነው??? ተዋንያኑ ይሄንን ባይሉትም እርግጠኛ ነኝ ይሄንን ዝግጅት በየቤታቸው ሆነው ከተመለከቱት ውስጥ ጥቂት የማይባሉ ሰዎች ይሄንን ጥያቄ ሳያነሡ አይቀሩም፡፡

ስለሆነም ጠያቂው ጥያቄ ሲጠይቅ ዝግጅቱ ለአእላፋት፣ ለተለያየ ዓይነት ተመልካች በብዙኃን መገናኛ መተላለፉን በማሰብ እንዲህ ዓይነት ነገሮችን ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ይጠበቅበታል፡፡ እርግጥ ነው ክርስቲያን ለሱስ እንዳይገዛ ቃሉ ያስጠነቅቃል፡፡ ሱስ ሲባል የመጠጥ ሱስ አለ፣ እንደተባለውም የጫት ሲስ አለ፣ የሲጋራ እና የሌሎች አደንዛዥ እጾችና መድኃኒቶች ሱስ አለ ወዘተረፈ. ይሄንን መሠረት በማድረግ ነው ጫትንና ሲጋራን አባቶች የሚከለክሉት፡፡ ይሁንና መጠጥ ከሱስ አማጭ ነገሮች አንዱ ቢሆንም የመጠጥ ሱሰኛ አትሁኑ ተባለ እንጅ መጠጥ ጨርሳቹህ አትጠጡ አልተባለም፡፡ ጌታ በቃና ዘገሊላ ዘርግ ቤት ሠራጊዎቹ የወይን ጠጅ ባለቀባቸው ጊዜ ስድስቱንም ጋኖቹን ውኃ አስሞልቶ በተአምር ውኃውን ወደ ወይን ጠጅ ለውጦ ያለቀውን ጠጅ በእጅጉ የሚያስንቅ፣ ከበፊቱ የበለጠና ሠርገኛው ሁሉ ያደነቀውን የወይን ጠጅ ሰጥቶ ሠራጊው እንዳያፍር ሠርገኛውም እስኪበቃው ተስተናግዶ እንዲሸኝ አድርጓል፡፡ ዮሐ. 2፤1-11,

ጌታ ራሱም ወይን ጠጅን ጠጥቶ በማሳየት ችግር እንደሌለው አሳይቷል ማቴ. 11፤19, ሐዋርያው ጳውሎስም ለመንፈስቅዱስ ልጁ ለጢሞቴዎስ "ለሆድህ ሕመም ጥቂት የወይን ጠጅ ጠጣ!" 1ኛ ጢሞ. 5፤23 ብሎታልና መጠጥ አብዝተን ጠጥተን እንዳንሰክርና የመጠጥ ሱሰኛ እንዳንሆን ሕግ ከለከለ እንጅ "መጠጥ ሱስ ያስይዛልና ፈጽሞ አትጠጡ!" አልተባለም፡፡

እንደዚሁም ሁሉ አባቶች "አትጠቀሙ ውጉዝ ነው!" የሚሏቸውን ጫትን፣ ሲጋራን፣ ቡናን ሌሎች ሱስ አማጭ ነገሮችን አንዳንድ ሰዎች "መጠጥን ሳንሰክርና በሱሱ ሳንያዝ እንደምንጠቀም፣ እንደተፈቀደልን ሁሉ እነኝህን ነገሮችንም በሱሳቸው ሳንያዝና ስካራቸው ውስጥ ሳንገባ መጠቀም እንችላለን!" የሚሉ አሉና መልስ ሲሰጥ የተለየ አመለካከት ያላቸውን ግለሰቦች ጥያቄዎች ግንዛቤ ውስጥ ባስገባና ለነሱም ምላሽ ሊሰጥ በሚችልበት መልኩ መሆን አለበት፡፡

ከመጠጥ ውጭ ያሉ ሱስ አማጭ ነገሮች (ለነገሩ ከመጠጥም ውስጥ አባቶች የሚከለክሉት መጠጥ አለ እሱም አረቂ ነው) ምክንያት አላቸው ወደኋላ እገልጸዋለሁ፡፡ እናም "መጠጥን በመጠን እንድንወስድ እንደተፈቀደልን ሁሉ ከመጠጥ ውጭ ያሉ ሱስ አማጭ ነገሮችንም በመጠን እንጠቀማለን!" ብሎ ሌሎቹንም ሱስ አማጭ ነገሮች መጠቀም አይቻልም፡፡

እርግጥ ነው መጽሐፍ ቅዱስ ብለን በምንጠራው መጽሐፍ እነኝህን ነገሮች መጠቀም "ኃጢአት ነው!" የሚል ቃል የለም፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለውም ሁሉም የጌታ ነው የተፈጠረውም በጌታ ነው፡፡ ነገር ግን ሁሉም የጌታና በጌታ የተፈጠረ ቢሆንም መቸም በጌታ የተፈጠረና የጌታ ነው ብለን መርዛማ ወይም ገዳይ የሆኑ እጽዋትንና እንስሳትን አንመገብም ወይም አንጠቀምም አይደል እንዴ? ቅዱስ ጳውሎስ የተናገረውን በደፈናው እንረዳው ካላቹህ መርዛማ ወይም ገዳይ ዕጽዋትንና እንስሳትንም እንመገብ እንጠቀም ልትሉ ነው፡፡ ከተመገብናቸው ደግሞ ለሞት ወይም ለአደጋ ልንዳረግ ነው፡፡

ስለሆነም ቅዱስ ጳውሎስ ማለት የፈለገው አንዳንዶቹ አሳስተው እንደተረዱት አይደለም ማለት ነው፡፡ እሱ ማለት የፈለገው እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ምግብነት ተስማሚ አድርጎ የፈጠራቸውን ማለቱ ነው ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም በምድራችን ካለው እንስሳትና እጽዋት ሁሉ ለሰው ልጅ ምግብነት ተስማሚ የሆነው ጥቂቱ ነው ሁሉም አይደለም፡፡ የተቀረው ደግሞ ተስማሚነቱ ለተቀሩት እንስሳት፣ አእዋፍና ዓሣት ነው እንጅ ለሰው ልጅ አይደለም፡፡ ከነሱም የአንዳቸው ለሌላኛቸው የማይስማማ

የማይሆን በርካታ ዕጽዋት እንስሳት አእዋፍና ዓሣት አሉ፡፡

በመሆኑም ቅዱስ ጳውሎስ ማለት የፈለገው እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ምግብነት ተስማሚ አድርጎ የፈጠራቸውን እንስሳት፣ አእዋፍ፣ ዕድዋትና ዓሣት ሁሉ ማለቱ ነው እንጅ በምድሪቱ ያለውን የሚገለውንም የማይገለውንም የሰውንም የእንስሳውንም ሁሉ ማለቱ እንዳልሆነ ይገባናል ብየ እገምታለሁ፡፡ አሁን ችግሩ ምድሪቱ ከያዘችው ጉልቆ መሳፍርት (ተቆጥሮ የማያልቅ) የዕጽዋት፣ የእንስሳት፣ የአእዋፍና የዓሣት ሀብት ሁሉ የትኞቹ ዕጽዋት፣ እንስሳት፣ አእዋፍና ዓሣት እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ምግብነት ተስማሚ አድርጎ እንደፈጠራቸው መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ተዘርዝረው አለመጠቀሳቸው ነው፡፡ እርግጥ ነው እንስሳትን አእዋፍን ዓሣትን በተመለከተ የትኞቹ ለሰው ልጅ ተስማሚ እንደሆኑ የትኞቹ እንዳልሆኑ በዝርዝር ተነግሯል ዘዳ. 14፤3-20 ይሁንና ስለ ዕጽዋት ወይም ፍራፍሬ ግን አልተገለጸም፡፡ እርግጥ ነው ሁሉም ዕጽዋት ይዘርዘሩ ቢባል ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ ትልቅ አዳራሽ የሚያክል ነገር ሊሆንና ለእኛም ለአያያዝ ለአጠቃቀም ፈጽሞ የማይመች ሊሆን ነው፡፡

በመሆኑም የትኛው ለሰው ልጅ ምግብነት ተስማሚና የተፈቀደ እንደሆነ፣ የትኛው ደግሞ የማይስማማና ያልተፈቀደ መሆኑን እየለየ እንዲጠቀም ለራሱ ለሰው ልጅ ኃላፊነቱ ተሰጠው ማለት ነው፡፡ በዚህ ሥልጣን መሠረት ነው አባቶች አንድን ክርስቲያን ክርስቲያናዊ ሕይዎቱንና ግዴታውን በአግባቡ እንዳይመራና እንዳይፈጽም የሚያደርጉትን፣ የሚያስተጓጉሉትን፣ ለአካላዊና አእምሯዊ ጤናው መቃወስ መንስኤ የሚሆኑትን ወይም ተስማሚ ያልሆኑትን፣ ከጤናማ አስተሳሰብ የሚያወጡትን ከሚያዩትና ከሚሰሙት እየለዩ "ይሄ ክልክል ነው እሱን የተጠቀመ ውጉዝ ነው!" በማለት በተሠጣቸው ሰማያዊና የማይታበል ሥልጣን ማቴ. 18፤18 ሲከለክሉ የምናያቸው፡፡

በዚህም መሠረት ነው ጫትን፣ ትምባሆን ወይም ሲጋራን፣ ቡናን፣ ሐሽሽን፣ ማሪዋናንና ሌሎች ሱስ አማጭ ነገሮችን እያወገዙ የሚከለክሉት፡፡ እንግዲህ ጫት፣ ቡና፣ ትምባሆ፣ ሐሽሽ ወዘተረፈ. ምግብነታቸውና ተስማሚነታቸው ለሌሎች እንስሳት ነው እንጅ ለሰው ልጅ አይደለም ማለት ነው፡፡ በመሆኑም እነሱን መጠቀም የቅዱሳን የአባቶችን ግዝት መተላለፍና ኃጢአት ነው ማለት ነው፡፡ ዜና ሥላሴ፣ ድርሳነ ጽዮን፣ ድርሳነ አርባዕቱ እንስሳት የተባሉ የቤተክርስቲያን ቅዱሳት መጻሕፍት ቡና የተከለከለና የተወገዘ የሰይጣን መጠቀሚያ ተክል እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ በትክክልም ቡና የሠይጣን መሥዋዕት፣ የሰይጣን መጠቀሚያ ነው፡፡ ለዚያም ነው ጠንቋንና ቃልቻ ቡናን ካላፈሉ ካላቀረቡ በስተቀር ሰይሳንን ወይም እርኩስ መንፈስን መሳብና መጠንቆል የማይችሉበት ያለቡና የማይሆንበት ምክንያት፡፡

ወደቀደመው ነገራችን እንመለስና ተዋንያኑ ጋባዡ ሲጠይቃቸው ትወና ላይ እያሉ ጫትና ሲጋራ እየተጠቀሙ ለመተወን ችግር እንደሌለባቸውና ከክርስትናቸው ጋር ችግር የሌለው መሆኑን እንደሚያስቡ ሲናገሩ ነው እነኝህ ሰዎች የክርስትና ሕይዎትና ሥራቸው ትወና ማለት ምን ማለት እንደሆነ ምንም እንደማያውቁ የገባኝ፡፡ እነኝህ ተዋንያን ትወናን በተመለከተ የዘነጉት ዐቢይ ቁምነገር ቢኖር ትወና ማለት አስመስሎ ማሳየት እንጅ ሆኖ ማሳየት ማለት አለመሆኑን ነው፡፡

ልብ ብለው አልተመለከቱትም እንጅ እራሳቸውን የሚያጠፉ ወይም ሰው የሚገሉ ገጸባሕርያትን ሲተውኑ እራሳቸውን እንዳጠፉ ወይም ሰው እንደገደሉ መስለው ይተውናሉ እንጅ የእውነት እራሳቸውን አጥፍተው ወይም ሰው ገለው አይደለም የሚተውኑት፡፡ ፊልም (ምትርኢት) ፣ ተውኔትና ድራማ (ትውንተ ኩነት) ላይ ከሌላ ሴት ጋር ጾታዊ ግንኙነት ያደርጉ አስመስለው ይተውናሉ እንጅ በትክክልም ግንኙነት እየፈጸሙ አይደለም የሚተውኑት፡፡ በዚህም መሠረት ጉንጫቸውን በደረቅ ዳቦ ወይም በጎመን ጎጥረው ጫት የሚያኝኩ ማስመሰል ይኖርባቸዋል እንጅ ጫት ማጨክ አይኖርባቸውም፡፡

ሲጋራውን በጣት ይዘው በካሜራ ትሪክ (በመቅረጸ ትዕይንት የማስመሰል ሥራ) ጭሱ ከሌላ ሲጋራ አጫሽ ሰው አፍ ሲወጣ በማሳየትና በማቀናበር የሚያጨሱ መስለው መተወን ይኖርባቸዋል እንጅ በትክክል ማጨስ አይኖርባቸውም፡፡ እንዲህማ ካሉ እራሱን የሚያጠፋና ከሌላ ሴት ጋር ወሲብ የሚፈጽም ገጸባሕርይን ሲተውኑም የእውነት እናድርገው ሊሉነው ማለት ነው፡፡ እንዲህ ቢያደርጉ በክርስቶስ ፊት በአመንዝራነትና በነፍስ አጥፊነት ቢከሰሱ ወይም ቢኮነኑ "አይ እኔ አይደለሁም እኮ የተባለው የተጫወትኩት ገጸባሕሪየ ነው ያደረገው!" ሊሉ ነው እንዴ??? ይሄስ ከፍርድ ነጻ የሚያወጣቸው ምክንያት ይመስላቸዋል??? እንዲያው ምን የዋሆች ናቸው ባካቹህ?

ባልኳቹህ መንገድ ሲጋራ የሚያጨሱና ጫት ያሚያመነዥኩ አስመስለውም እንኳ መተወን የሚኖርባቸው የሚሠሩት ምትርኢት፣ ተውኔትና ትውንተ ኩነት የሚያንፅ ከሆነ ነው እንጅ እንደምናየው ከሥነምግባር፣ ከግርረገብ፣ ከሃይማኖት፣ ከዜግነት ግዴታ ወዘተረፈ. መመዘኛዎች አንጻር ሲመዘን ምንም ዓይነት ፋይዳ ለሌለው፣ ትውልዱን ምን ሊያስተምር እንደፈለገ እንኳን ለተመልካች ራሱ የምትርኢቱ፣ የተውኔቱ፣ የትውንተ ኩነቱ ጸሐፊ እንኳ በውል ለማያውቀው ምትርኢት፣ ተውኔትና ትውንተ ኩነት አንድ ክርስቲያን ክርስቲያናዊ ሕይዎቱን በሚፃረር መልኩ መተወን የለበትም፡፡

ተዋንያኑ እንደገለጹት ዕኩይ ገጸባሕርይን በሚጫወቱበት ጊዜ በሚጫወቱት ዕኩይ ገጸባሕርይ ምክንያት ሃይማኖትን ላለማስነቀፍ ላለማስተቸት መፍትሔ አድርገው እየወሰዱት ያሉት እርምጃ ያሉት ማተብን ፈትቶ መጫወትን ነው፡፡ ይሄ ደግሞ ወይ አንገታቸው ሊታይ የማይችልበትን ዘዴ ቢጠቀሙ ካልሆነም ማተባቸው እየታየ ቢተውኑ ይሻላል እንጅ ማተብን መፍታት በቤተክርስቲያን ሥርዓት ፈጽሞ የተከለከለ ነው፡፡ አንድ ክርስቲያን በአርባና በሰማንያ የሥላሴን ልጅነት ካገኘ ጊዜ ጀምሮ ለአንድ አፍታም እንኳ ቢሆን አንገቱ ያለማተብ ሊሆን የተገባ አይደለም፡፡ ማኅተመ መንፈስቅዱስን እንዳራቀ ነው የሚቆጠረው፡፡ ክርስቲያን ሲሞት እንኳ ማተቡ አይፈታም ከነማተቡ ነው የሚቀበረው፡፡ እየተጫወቱት ያሉት ጸገባሕርይ ትወና እንደሆነ ለማንም ግልጽ ስለሆነ ማተባቸውን ሳይፈቱ ቢጫወቱ ይሻላል ከሚፈቱ፡፡ ሰይጣን ጥበበኛ ነው ብቻ በሰበብ አስባቡ ቀኖና ቤተክርስቲያንን እያስጣሰ ለጉዳት ይዳርገናል፡፡

ይገርማቹህል እኔ በግሌ ከምታደንቀው ሞያ ሁሉ ጥቀስ ብባል የምጠቅሰው ሞያ ትወናን ነው፡፡ ትወና እጅግ ጉልበት አስጨራሽና የመጨረሻ አቅም ጠያቂ ሥራ ነው፡፡ የትወናን ያህል አቅም አስጨራሽና አድካሚ ሥራ ያለ አይመስለኝም፡፡

የዛኑ ያህል ደግሞ እጅግ የምትጠላውና የምትጸየፈው ሥራ ምንድን ነው ብትሉኝ አሁንም "ትወና!" ነው የምላቹህ፡፡ ተዋናይነት ፈጽሞ እራሳቹህን እንድትሆኑ ዕድል የማይሰጥ አስቀያሚ ሞያ ነው፡፡ ተዋኝ ወይም ተዋናይ ስትሆኑ ገጸ ባሕርያት በሕይዎታቹህ ውስጥ ጣልቃ እየገቡ እያረከሱ፣ እያበላሹ፣ እያቆሸሹ ሕይዎታቹህን እንደፈለጉ ያመሰቃቅሉላቹሀል፡፡ አንድ ተዋኝ ዕኩይ ገጸባሕርያትን አልተውንም! ሠናይ ገጸባሕርያትን ብቻ ነው የምተውነው ካላለ በስተቀር ከዚህ ሊያመልጥ አይችልም፡፡

አንድ ምሳሌ ልስጣቹህ ሽዋዚንገር የሚባል የሆሊውድ ተዋናይ ታውቃላቹህ፡፡ በፊልም (በምትርኢት) ቀረጻ ላይ እያለ ወሲብ እየፈጸመ በሚያስመስልበት የቀረጻ ትዕይንት ላይ ስሜት ውስጥ እየገባ በርካቶችን ረዳት ተዋንያንን እዛው ላይ ተገናኝቷቸዋል፡፡ ለጊዜው በገንዘብ ኃይልና በማስፈራራት ዝም ቢያሰኛቸውም ለከንቲባነት በተወዳደረ ጊዜ ግን ወደ ዐሥር የሚሆኑት ጉዱን ለአደባባይ አብቅተውበት ውድድሩ ላይ ችግር ተፈጥሮበት ነበር፡፡ አስቡት እንግዲህ የሱን ተውትና የደፈራቸው ረዳት ተዋንያን ማንነት፣ ሕይዎት፣ ክብር አልረከሰም? አልጎደፈም? አልተበላሸም? አልተዋረደም ወይ??? ባለትዳሮች ቢሆኑስ?

በዚህም ምክንያት ነው በምዕራቡ ዓለም፣ በኛም ሀገር ቢሆን፣ በሌሎቹም ሀገራት እንዲሁ ተዋንያኑ አርአያነት ያለው የተረጋጋ ሕይዎት ሊኖራቸው የማይችለው፡፡ ተመልካችን ለማሳመን በሚል ሰበብ በሚፈጠር ከልክ ያለፈ የትወና ድርጊት ለመሰናከል ምክንያት እየሆነ ለትዳራቸው ታማኝ ለመሆን የማይችሉትና የትዳር ጉድኝታቸው የማይጸናው ባጠቃላይ ሕይዎታቸው ብልሽትሽት ያለና ለአርአያነት የማይበቃው ለዚህ ነው፡፡ ብቻ ምን አለፋቹህ ትወና ትንሽ ከበድ የሚል ሥራ ነው፡፡ አብሶ ለክርስቲያን ፈጽሞ የማይሆን ሥራ ነው፡፡

በዚሁ አጋጣሚ ለይገረም አንድ መልእክት ላስተላልፍ፡፡ ዘንድሮ የጌታ ልደት ዕለት ይገረም በማኅበራዊው የብዙኃን መገናኛ የለቀቀው አንድ የልደት መዝሙር ነበረ፡፡ ይገረም በክርስቲያናዊ ሕይዎቱ አርአያ መሆን ከቻለ መዘመር መብቱ ነው፡፡ እኔ ይገረም ይሄ አርዓያነት ይኑረው አይኑረው የማውቀው ነገር የለኝም፡፡ ነገር ግን በቅርቡ በኢቢኤስ አንድ ዝግጅት ላይ ጥቁር አንበሳ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትን በተመለከተ እሱ የትምህርት ቤቱ ተማሪ ስለነበር ትዝታውን ሲያጋራ እዚያ ት/ቤት ተማሪ እያለ ከአንዷ ተማሪ ከጋብቻ ውጭ ልጅ መውለዱን፣ እሱና ጓደኞቹ ተደባዳቢና የማይደፈሩ እንደነበሩ ሲናገር ሰምቸው ነበረ፡፡

እንዲህ ዓይነት ሕይዎት የነበረው ሰው ምን ተሰጥኦና ፍላጎት ቢኖረው ለራሱ በቤቱ እየዘመረ አምላኩን ማመስገን ይችላል እንጅ በቤተክርስቲያን ዐውደ ምሕረት ቆሞ ልብሰ ተክህኖ ለብሶ በመዝሙር ማገልገል አይችልም፡፡ በእርግጥ ንስሐ የማያጸዳው ሐጢአት የለም፡፡ ይገረም ለኃጢአቱ ተገቢውን ንስሐ ወስዶ በንስሐ ሕይዎት ውስጥ ሆኖ ከሆነ በመዝሙር እያገለገለ ያለው መዘመር መብቱ ነው፡፡ ነገር ግን "በገጸባሕርይ ላይ ሆኘ ከሆነ ጫት ብቅምና ሲጋራ ባጨስ ክርስትናየ ላይ ምንም የሚያመጣው ችግር የለም!" ብሎ ከተናገረው ተነሥቸ ስገምት ይገረም በተገቢው የንስሐ ሕይዎት ውስጥ መሆኑን በእጅጉ እጠራጠራለሁ፡፡

የገረመኝ ነገር ይገረም የጌታ ልደት ቀን ለቀቀው ባልኳቹህ መዝሙር ላይ ይገረም ከመቅደሱ በር ላይ ቆሞ ካባ ደርቦ የዲያቆኑን አክሊል አጥልቆ ሲዘምር ይታያል፡፡ ይገረም የመዝሙር አገለግሎትን ትወና አድርጎት ነው መሰለኝ ወይም ካለማወቅ ይህ ከቀኖና ቤተክርስቲያን ውጭ የሆነ ድርጊቱ ምንም አልከበደውም፡፡ መቸም አባቶች ባያዩት ወይም ደግሞ ክህነት ያለው መስሏቸው ይሆናል እንጅ በምንም ተአምር ቢሆን ዝም የሚሉት አይመስለኝም፡፡

ለነገሩ ዛሬ ምን አባት አለና ማን ምን ይላል? ይሄንኑ የዲያቆን አክሊል ሴት የሰ/ት/ቤት ተማሪዎች ሳይቀር አድርገው ሲዘምሩ እያዩዋቸው አይደለም እንዴ ዓይተው እንዳላዩ ሆነው እያለፏቸው??? ለበረከት ብለው የመጡትን ልጆች ለቅስፈት እየዳረጓቸው ያሉት??? በቤተክርስቲያናችን ሥርዓትና ቀኖና መሠረት አንድ ዲያቆን ያልሆነና ክህነት የሌለው ሰው የዲያቆንን አክሊልና ልብሰ ተክህኖ በፍጹም ማድረግ መልበስ አይችልም፡፡ ቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉ አልባሳት በሙሉ እንደ ሥልጣነ ክህነቱ ማን የቱን እንደሚለብስ ሕግና ሥርዓት አለው፡፡ ማንም አንሥቶ ሊለብሰው አይችልም፡፡ ቤተክርስቲያን ውስጥ ያለ ሥልጣነ ክህነት የሚለበስ ልብሰ ተክህኖ የለም፡፡

ዲያቆኑ እንኳ እራሱ የካህኑን አክሊልና ልብሰ ተክህኖ ማጥለቅና መልበስ አይችልም፡፡ ቄሱም የመነኩሴውን ቆብና ቀሚስ ማድረግ አይችልም፡፡ መነኩሴውም የጳጳሱን ማጥለቅ አይችልም፡፡ የዲያቆኑ፣ የቄሱ፣ የመነኩሴውና የጳጳሱ አክሊል፣ ቆብና አስኬማ ክብራቸውንና ደረጃቸውን በሚገልጽ መልኩ የተለያየ ነው፡፡ ዲያቆኑ ጽንሐው ላይ ፍም እንዲጨምር ሲላክ እንኳ ወረድ ብሎ የጽንሐውን ሰንሰለት ወይም ሻኩራ ይዞ ፍሕሙን ይጨምራል እያወዛወዘም ያቀጣጥላል እንጅ የጽንሐውን እጀታ እንዲይዝ ፈጽሞ አይፈቀድለትም፡፡ ምክንያቱ ምንድን ነው ያላቹህ እንደሆን የእሱ ክህነት ዲቁና እንጅ ቅስና ስላልሆነ ነው፡፡

እናም በቤተክርስቲያን ሁሉም ነገር ሥርዓትና ቀኖና አለው፡፡ ማንም እየዘለለ እየገባ እንደፈለገ የሚያደርገው ምንም ነገር የለም፡፡ እንዲያውም ይሄ የአለባበስ ጉዳይ ሰባኪ ነኝ፣ ዘማሪ ነኝ፣ የሰ/ት/ቤት ተማሪ ነኝ በሚሉ ግለሰቦች ሥርዓቱና ቀኖናው ተጥሶ ፈራርሶ እጅግ አሳሳቢ ደረጃ ላይ የደረሰበት ደረጃ ላይ ስለሆነ ያለነው በሚቀጥለው ጊዜ በጥልቀት ብመለስበት ይሻላል ጠብቁኝ፡፡

እናም ይገረም ዘመኑ እግዚአብሔር ብዙ የሚታገስበት ስምንተኛው ሺህ ሆነ እና ተረፈ እንጅ በጥንት በሊቀ ነቢያት በሙሴ ወይም በዖዝያን ዘመን ቢሆን ኖሮ ይገረም የዲያቆኑን አክሊል አጥልቆ ካባውን ደርቦ መቅደሱ በርላይ እንደቆመ ተቀስፎ ሞቶ ነበረ፡፡ እናም መዳፈሩ ይቅር አይጠቅምም ነው መልእክቱ፡፡

ሌላው ደግሞ ተዋኝ ንብረት ገላው "የእኛ ቤተክርስቲያን በትክክለኛው መንገድ የኢየሱስን ጨምሮ መንፈሳዊ ፊልሞችን (ምትርኢቶችን) መሥራት ይኖርባታል!" ባለው ላይ አንድ ሐሳብ ልሰንዝርና ጽሑፌን ልቋጭ፡-

በምሥራቅ አቢያተክርስቲያናት ማለትም በኢትዮጵያ፣ በግልጽ፣ በሶሪያ፣ በአርመንና በሕንድ አቢያተክርስቲያናት ቀኖና መሠረት ክርስቶስንም ሆነ ቅዱሳንን መስሎ መተወን የተከለከለ የተወገዘ ነው፡፡ በካቶሊክና በፕሮቴስታንት ግን ክርስቶስንም ሆነ ቅዱሳንን መስሎ መተወን ይቻላል፡፡ ይሁንና የግብጽ ቤተክርስቲያን ቀኖናውን በማሻሻል የትወናውን ዓለም ተቀላቅላለች፡፡ እኛም ብንሆን የምትርኢት ትወናውን እስከአሁን ባንቀላቀልም የተውኔቱን ትወና ግን በየሰንበት ት/ቤት በሚሠሩት ተውኔቶች ከተቀላቀልነው ቆይተናል፡፡ ስሕተት በመሆኑ መቆም ይኖርበታል፡፡ ከታች የጠቀስኳቸውን ነጥቦች በመጠንቀቅ ልብ ወለድ የሆኑ አስተማሪ ድርሰቶችን መተወን ግን ችግር የለውም፡፡

በነገራችን ላይ የምሥራቅ አቢያተክርስቲያናት (oriental churches) በትወና ብቻ ሳይሆን በሥነ ሥዕልም የገደብ ቀኖና አላቸው፡፡ ሥዕለ አድኅኖዎቹ የሚጨበጡ የሚዳሰሱ (realistic) መስለው እንዲሣሉ አይፈቀድም፡፡ ደምበኛ ወይም የሚጨበጥ የሚዳሰስ ሳይመስል በምሳሌያዊ (figurative) ደረጃ የተወሰነ ነው የሥዕለ አድኅኖ ቀኖናችን፡፡ ይሄ ቀኖና ግን ብዙ አላገለገለም በራሱ ጊዜ ከተለወጠ ወይም ከተሻሻለ ቆይቷል፡፡ መለወጡ ወይም መሻሻሉም ትክክል ነው፡፡ ለድሮው ዘመን ግን መሆን የነበረበትና ትክክልም ነው፡፡ ምክንያቱ ብዙ ስለሆነ ወደሱ አልገባም፡፡

አክራሪ የሚባሉት የምሥራቅ አብያተክርስቲያናት በቀኖናቸው ክርስቶስንም ሆነ ቅዱሳንን መስሎ መተወን የከለከሉበት ምክንያቶች 4 መሠረታዊ ምክንያቶች አሉ፡-

1ኛ. ክርስቶስ ወይም ቅዱሳን ያሳለፉትን ሕይዎት አስመስሎ መተወን ፈጽሞ ስለማይቻል ሕይዎታቸውን ተጋግሏቸውን ያሳያል ያስተምራል የተባለው ትወና ክርስቶስ ወይም ቅዱሳኑ ያሳለፉትን መከራና ተጋድሎ አስመስሎ ማቅረብ ካለመቻሉ የተነሣ በተቃራኒው ተጋድሏቸውን አቃልሎ በማቅረብ የክርስቶስን ወይም የቅዱሳኑን ሕይዎት መከራ ተጋድሎ በትወናው ላይ የታየውን ያህል ብቻ እንደሆነ አስመስሎ በሰዎች ሕሊና በመሳል ተጋድሏቸው ቀሎ እንዲታይ ስለሚያደርግ፡፡

2ኛ. ክርስቶስን ወይም ቅዱሳኑን መስለው የሚተውኑት ተዋንያን ሕይዎት ቅድስና የተለየው፣ በኃጢአት የተሞላ ከሆነ ይሄ ማንነታቸው በሕዝበ ክርስቲያኑ ስለሚታወቅ ክርስቶስን ወይም ቅዱሳኑን መስለው በሚተውኑበት ሰዓት በተመልካች ዘንድ ትክክለኛ ማንነታቸው ከገጸባሕርይው ጋር ግጭት ስለሚፈጥርና በቀና ለመመልከት ስለማያስችል በዚህ ምክንያት የሚያንጽ ስለማይሆን፣ የምዕመናኑን ሕሊና የሚኮሰኩስ የሚሻክር ስለሚሆን፣ የመደፈር ስሜትን ስለሚፈጥር፡፡

3ኛ. መልካምና አርአያነት በሌላቸው፣ የቅድስና ሕይዎት በሌላቸው ተዋንያን ክስርቶስንም ሆነ ቅዱሳኑን መስሎ መተወን የክርስቶስንም ሆነ የቅዱሳኑን ክብር ስለሚነካና አግባብም ስላልሆነ ነው፡፡ ለምሳሌ ጅሰስ በተሰኘው የምዕራባውያኑ የኢየሱስ ፊልም (ምትርኢት) ኢየሱስን ሆኖ የሚተውነው ሰው ሮበርት ፓውል በእግዚአብሔር የማያምንና ሱሰኛ ሰው ነው፡፡ እንኳንና በእንዲህ ዓይነት ሰው መልካም ሥነምግባር ባለው ወይም ቅድስና ባለው ክርስቲያን እንኳ ቢሆን አምላክን ክርስቶስን በሰው መስሎ መተወን ምን ያህል መዳፈር እንደሆነ ለማንም ግልጽ ይመስለኛል፡፡

4ኛ. ክህነትን የሚጠይቁ መንፈሳዊ አገልግሎቶች ለተውኔት ወይም ለምትርኢት ሥራ በሚል በትወና በተጨማሪም ክህነት በሌለው ሰው ልብሰ ተክህኖን በመጠቀም መተወን ፈጽሞ የማይቻል የማይፈቀድም በመሆኑ፣ በመንፈስቅዱስና በጸጋው ላይ መቀለድ መሳለቅ በመሆኑ ከዚህ የተነሣ ፈጽሞ የተከለከለ ስለሆነ ነው፡፡

እነኝህ ምክንያቶችም እውነትና መጠበቅም ያለባቸው በመሆናቸው የምሥራቅ አብያተክርስቲያናት በዘመናዊነት እየተዋጡና እየተማረኩ እየተዋቸው እየመጡ ነውና ቅዱሳን አባቶች ያስቀመጡትን ቀኖና ባይተው፣ ቅጽር ባያፈርሱ መልካም ነው፡፡ መዳፈሩ ቅስፈትን እንጅ በረከትን ወይም አንዳችም የሚረባ ነገር ጠብ አያደርግምና፡፡ ይመስለናል እንጅ ተዳፍረን የምንሠራው ሥራ ማንንም ሊያንጽ አይችልምና፡፡

ወስብሐት ለእግዚአብሔር ወለ ወላዲቱ ድንግል ወለመስቀሉ ክቡር አሜን!!!

ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው
amsalugkidan@gmail.com